# ስደት በአዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ በዶ/ር አብይ ዘመን ሰዎች እየተፈናቀሉ ቤታቸው እየተቃጠለ ማየት እየተለመደ መጥቷል። የሚገርመው ግን አንድ የደካማ ቤት መንግስት ሰርቶ በየሚዲያው ፕሮፓጋንዳው ሌላ ነበር። በየሰፈሩ ሰዎች ያለምንም ተተኪ መኖሪያ፣ ቤት አልባ እየተደረጉ ብዙዎች ሲፈናቀሉ ምንም እንዳልሆነ የመንግስቱም ሆነ የተደመረው ሚዲያ ፀጥ ይላል። የሰው ሰውነት የሚለካው ለሰው ልጅ መብት ሲቆም ነው። ሰዎችን ቤት አልባ ማድረግንና ቤት አልባነትን ያውም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ምንም እንዳልሆነ "ጆሮ ዳባ ልበስ" ማለት በጣም ያሳዝናል። ህፃናትና ደካማ ቤተሰብ ያላቸውን ቤተሰቦች በዋና ከተማችን ጎዳና ተዳዳሪዎች እንዲሆኑ እየተደረገ፣ የሰው ልጅ የመኖር መብት እየተጣሰ፣ ስለሰው ልጅ መብት ሳይጠይቁ፣ ባለስልጣኖቹም አፍንጫቸው ስር መከራ ላይ የወደቀውን ህዝብ መፍትሄ ሳይሰጡ፣ ስለመደመር ብቻ መዘመር ትክክል አይመስለኝም።

**ስ**ደት በአዲስ አበባ - በነአብይ ጊዜ

**ደ**ርሶ አይናችን አየ - በሀዘን በትካዜ

**ት**ርጉም አጣ ህይወት - በንቀት አባዜ

**በ**ደሉ ቅጥ አጣ - ከጎጆ መባረር

**አ**ንዳንዱ ተጠርቶ - ሲሰፍር በክብር

**ዲ**ሞክራሲ መጣ - ብሎ ተደስቶ

**ስ**ንቱ ተፈናቅሎ - ቤቱ በሳት ጋይቶ

**አ**ዲስ አበባ ላይ - ሰው ግራ ተጋብቶ

**በ**ትውልድ አገሩ - ፍትህ ተዛብቶበት

**ባ**ከነ አዲሳቤ - ከንቲባ ባለበት።







ዘውዲቱ የማነ

2019-02-03